የሰ/መ/ቁ. 52075

ታህሳስ 26 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገብረሥላሴ

ብርሀኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ጌቱ ብርሀኑ - የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** የፌዴራል ዐቃቤ ህግ - ወርቅነህ ዘነበ ቀርበዋል፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የበታች ፍርድ ቤት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪ አመልካች በወንጀል ህግ አንቀፅ 543 ንዑስ አንቀፅ 2 የተመለከተውን በመተላለፍ ግንቦት 22 ቀን 1998 ዓ.ም ከጧቱ ሁለት ሠዓት የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02/03 የሰሌዳ ቁጥር 3-17408 አ.አ የጭነት መኪና ከአየር ጤና ወደ ቃሊቲ አቅጣጫ በማሽከርከር ላይ እንዳለ ገብሬል ቤተክርስቲያን ፊት ለፊት ሲደርስ ከመኪናው ላይ አሣፍሮት የነበረው ታምራት ሰማኸኝ ከመኪናው ወድቆ በመሞቱ በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል ፈፅሟል በማለት ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ነው፡፡ አመልካች ጥፋተኛ አይደለሁም ብሎ በመከራከሩ ተጠሪ ሁለት ምስክሮች አቅርቦ አሰምቷል፡፡ የተጠሪ ምስክሮች ሟች አመልካች የቆመለት መስሎት ለመውረድ ሲሞክር አመልካች መኪናውን በማሽከርከሩ ሟች ወድቆ የሞተ መሆኑንና አመልካች ከላይ የተጫነው ሰው ሁኔታ በስፖኪ ሣያይና ሣያረጋግጥ ማሽከርከሩ በሙያው ማድረግ የሚገባውን ጥንቃቄ ያላደረገ መሆኑን ያሳያል በማለት መስክረዋል፡፡ አመልካች የመከላከያ ማስረጃ የሌለው መሆኑን ለሥር ፍርድ ቤት አረጋግጧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች የወንጀል ህግ አንቀፅ 543 ንዑስ አንቀፅ 2ን በመተላለፍ በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ነው በማለት አመልካች በአንድ ዓመት ከሶስት ወር ቀላል እስራትና በብር 4500 መቀጮ እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ቢሆንም ይግባኝ ሰሚው ችሎት የአመልካችን ይግባኝ አልተቀበለውም፡፡

አመልካች ጥር 10 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የተጠሪ ምስክሮች ቃል በአይናቸው ያረጋገጡት ፍሬ ጉዳይን የመሰከሩ ሳይሆኑ የራሳቸውን ሀሳብ የገለፁ ናቸው፡፡ አመልካች ሟችን በሚያሽከረክረው መኪና ላይ አልጫነም ሀላፊነት ወስጄ ያልጫንኩትን ሰው ህይወት ደህንነት ጥንቃቄ ላደርግ አልችልም ስለዚህ የአመልካች ድርጊቱ በወንጀል ህግ አንቀፅ 543 ንዑስ አንቀፅ 2

የሚሸፈን አይደለም፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ሟች ተጠሪ ሲያሽከረክረው ከነበረው መኪና ላይ ወድቆ የሞተ መሆኑን በማስረጃ አስረድተናል፡፡ አመልካች ሟችን አለመጫኑን በመከላከያ ማስረጃ አላረጋገጠም፡፡ የአመልካች አድራጎት የትራንስፖርት ደንብ ቁጥር 279/56ን የሚጥስና በሙያው ማድረግ የሚገባውን ጥንቃቄ ባለማድረጉ የሟች ህይወት ለህልፈት የበቃ መሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ ውሣኔው መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች በፈፀመው ጥፋት የሆነ ቸልተኝነት ከሚያሽከረከረው መኪና ላይ አሣፍሮት የነበረው ሟች ታምራት ሰማኸኝ የሞት አደጋ የደረሰበት መሆኑን ተጠሪ በቂ ማስረጃ በማቅረብ ያረጋገጠ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የከፍተኛው ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ አመልካች የተጠሪን ማስረጃ ለመከላከል ያቀረበው ማስረጃ የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ፍሬ ጉዳይ በማጣራትና ማስረጃ በመመዘን ሂደት ፈፅመውታል የሚለውን ስህተት ይህ ሰበር ችሎት እንዲያርምላቸው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ለሰበር ችሎት በህገ መንግስቱ አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀፅ 3(ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 የተሰጠውን ሥልጣን ከግንዛቤ ውስጥ ያላስገባ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ አመልካች ከመኪናው ላይ አሳፍሮት የነበረው ሟች ከመኪናው እየወረደ እያለ መኪናውን ጥንቃቄ በጎደለው ሁኔታ በማሽከርከሩ ሟች ከመኪናው ላይ ወድቆ ለህልፈት የተዳረገ መሆኑን በሥር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም የአመልካች አድራጎት በወንጀል ህግ አንቀፅ 543 ንዑስ አንቀፅ 2 የተደነገገውን መሥፈርት የሚያሟላ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 195(1/ለ-2) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. ውሣኔው የፀና መሆኑን አውቆ ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ለአዲስ አበባ ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ይፃፍ፡፡

   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡*

ራ/ታ